DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

የካቲት 11 ቀን 2016 ዓ.ም.

ውድ ወላጆችና ቤተሰቦች፡

ይህን ደብዳቤ መላክ ያስፈለገበት ምክንያት፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የከተማው የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE) የካቲት 9 ቀን 2016 ዓ.ም. ለዲሲ ካውንስል የ2015 ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ምላሽ በሰጠበት የቀጠሮ ቀን ልዩ ማንነትን የሚገልጽ የተማሪ መረጃ በመሰጠቱ ነው። ይህ በስህተት የተሰጠው የመረጃ ስብስብ ልዩ የተማሪ መግለጫዎችን (USIs)፣ ስሞችን፣ ዕድሜዎችን፣ የክፍል ደረጃን፣ ዘርን፣ የአካባቢ የትምህርት ድርጅትን (LEA)፣ የተማሩበትን ትምህርት ቤት፣ የአካል ጉዳተኝነት ምድቦችንና የ12,000 የዲስትሪክቱ ተማሪዎች ግላዊ የትምርሀት እቅድ (IEP) አገልግሎቶችን ይጨምራል። <u>የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥሮችና የልደት ቀናት በዚህ መዝገብ ላይ **አልገቡም**።</u>

የOSSE ፋይሎችን - በተለይ ከዚህ ጉዳይ ጋር የተያያዙ ፋይሎችን - ማግኘት በመጠኑ የተወሰነ እንደሆነ ብናምንም፣ ይህ ድንገተኛ ክስተት መሆን የማይገባው ነበር። ይህንን በተመለከተ የሚከተሉትን እርምጃዎች ወስደናል፡

- ወዲያውኑ ሁለቱን ፋይሎች ከድህረ ገጹ ላይ አጥፍተናል።
- ሌሎቹን ፋይሎች በሙሉ መርምረን በስህተት ሌላ መረጃ ይፋ እንዳይሆን አረጋግጠናል።
- ለከንቲባዋ የአስተዳደር ቢሮ እና ለLEA መሪዎች ሪፖርት አድርገናል።
- ይህን የመሰለ ሌላ ሁኔታ ወደፊት እንዳይከሰት የድርጅቱን የመረጃ ስብስብ ፖሊሲ ላይ የተሟላ ግምገማ አድርገናል።

ቤተሰቦች ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ የሚደውሉበት አፋጣኝ የስልክ መስመር (202) 481-3400 እንዲሁም የኢሜል አድራሻ፡ osse.studentprivacy@dc.gov አዘጋጅተናል።

የልጅዎ ማንነት ሚስጥራዊነትና የግል መረጃ በጣም አስፈላጊ መሆኑን እናውቃለን፣ ስለሆነም፣ ስለተደረገው ሁኔታ ጥልቅ የሆነ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ይህ መሆን አይገባውም ነበር፣ ስለዚህ የልጅዎን ደህነትና ሚስጥራዊ መረጃ ለመጠበቅና እንደዚህ ዓይነት ያልታሰበ ሁኔታ ለወደፊት እንዳይፈጸም ለመከላከል የሚገባንን ጥረት ለማድረግ ቃል እገባለሁ።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ምንም ዓይነት ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት፣ ወይም መረጃው የተገለጸበትን ተማሪ የተመለከተ መረጃ ከፈለጉ፣ በአፋጣኝ የስልክ መስመሩ በ(202) 481-3400 ይደውሉ ወይም በኢሜል osse.studentprivacy@dc.gov ይላኩልን።

ከሰላምታ ጋር

ሃንሴዉል ካንግ
የከተማው የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ